- እግዚአብሔር ምግብ የማያስፈልገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚኖረው በራሱ ኃይል ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር መጠጣት የማያስፈልገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚኖረው በራሱ ኃይል ስለሆነ ነው።

- መሬት ወይም ፀሐይ ባይኖር መኖር ትችላላችሁ?

- አትችሉም እግዚአብሔር ግን ይችላል።



ትምህርት 2

1. እዚህ የመጣሁት ለምንድነው?
ሀ- በዚህ ዓለም እጅግ አስፈላጊ የሆነውን መልእክት ልነግራችሁ ነው።

2. በዚህ ዓለም እጅግ አስፈላጊ የሆነው መልእክት?
ሀ- የእግዚአብሔር መልእክት ነው።

3. የእግዚአብሔር መልእክት በዚህ ዓለም እጅግ አስፈላጊ መልእክት የሆነው ለምንድን ነው?
ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር በፍጹም ስለማይዋሽ ነው።
ለ- እግዚአብሔር ሁል ጊዜ እውነትን ብቻ ስለሚናገር ነው።

4. የእግዚአብሔር መልእክት የሚገኘው የት ነው?
ሀ- የእግዚአብሔር መልእክት የሚገኘው በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ ነው።

5. የእግዚአብሔር መጽሐፍ ምን ይባላል?
ሀ- የእግዚአብሔር መጽሐፍ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ይባላል።

6. የእግዚአብሔር መልእክት በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ እንዴት ተጻፈ?
ሀ- ከረጅም ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ጥቂት ሰዎችን መረጠ ቃሉንም በእነዚህ ሰዎች ልብ ውስጥ አኖረ።
ለ- ከዚያም እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ ጻፉት።

7. እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ የጻፉት የራሳቸውን ቃል ነው?
ሀ- የራሳቸውን ቃል አይደለም።
ለ- እነዚህ እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች የጻፉት በትክክል የእግዚአብሔርን ቃል ነው።

8. እነዚህ የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉት ሰዎች ሁሉም የኖሩት በተመሳሳይ ጊዜ ነበር?
ሀ- አይደለም።

9. ሁሉንም የእግዚአብሔር ቃል ጽፎ ለማጠናቀቅ ምን ያህል ጊዜ ፈጀ?
ሀ- እነዚህ እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች ቃሉን ጽፈው ለማጠናቀቅ 1,600_ዓመታት ፈጅቶባቸዋል።

10. እነዚህ እግዚአብሔር ቃሉን እንዲጽፉ የመረጣቸው ሰዎች እነማን ነበሩ?
ሀ- እግዚአብሔር ቃሉን እንዲጽፉ የመረጣቸው ሰዎች አይሁዶችና አንድ ግሪካዊ ነበሩ።

11. እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉት በምን ቋንቋ ነበር?
ሀ- በአይሁዶችና በግሪኮች ቋንቋ ነበር።

12. በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል መካከል ስንቱ እውነት ነው?
ሀ- ሁሉም እውነት ነው።

13. በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው ሁሉም የእግዚአብሔር ቃል እንዴት እውነት ሊሆን ቻለ?
ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር በፍጹም ስለማይዋሽ ነው።
ለ- እግዚአብሔር እውነትን ብቻ ስለሚናገር ነው።

- እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ እንዲጻፍ ያደረገው የመጀመሪያው ቃል ምን የሚል ነው?

- እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ እንዲጻፍ ያደረገው የመጀመሪያው ቃል

- «በመጀመሪያ» የሚል ነው።

- እግዚአብሔር ቃሉን «በመጀመሪያ» በሚል ለምን ጀመረ?



- እግዚአብሔር ያልነበረበት ጊዜ ነበር?

- አልነበረም።
- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ነበር።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜም አለ።
- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይኖራል።

- እግዚአብሔር ያልነበረበት ጊዜ ፈጽሞ አልነበረም።

- እግዚአብሔር በጭራሽ ሊሞት አይችልም።

- እግዚአብሔር በጭራሽ ሊርበው አይችልም።
- እግዚአብሔር በጭራሽ ሊጠማው አይችልም።

- ሰዎች ለመኖር ምግብና ውሃ ያስፈልጋቸዋል እግዚአብሔር ለመኖር የሚያስፈልገው ምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ለመኖር ምንም አያስፈልገውም።

- ታዲያ እግዚአብሔር የሚኖረው እንዴት ነው?
- እግዚአብሔር የሚኖረው በራሱ ኃይል ነው።

- እግዚአብሔር ለመራመድ ምድርን የማይፈልገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚኖረው በራሱ ኃይል ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር ለማየት የፀሐይን ብርሃን የማያስፈልገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚኖረው በራሱ ኃይል ስለሆነ ነው።

- ሰዎች ስለ መጀመሪያ ሊነግሩን የማይችሉት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ከመጀመሪያ በፊት ሰዎች ስላልነበሩ ነው።

- መናፍስት ስለ መጀመሪያ ሊነግሩን የማይችሉት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ከመጀመሪያ በፊት መናፍስት ስላልነበሩ ነው።

- እግዚአብሔር መኖር የጀመረው መቼ ነው?
- እግዚአብሔር መጀመሪያ የለውም።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይኖራል።
- እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው።

- እግዚአብሔርን የፈጠረው ይኖር ይሆን?
- የለም።

- እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው።

- አንዳንዶች «እግዚአብሔር ራሱን ፈጠረ» ብለው ያስባሉ።

- እግዚአብሔርን የፈጠረው ራሱ እግዚአብሔር ይሆን?
- አይደለም።

- እግዚአብሔር አልተፈጠረም አልተወለደም።
- እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው።



- ምክንያቱም ሁሉም ነገር መጀመሪያ እንዳለው እንድናውቅ እግዚአብሔር ስለሚፈልግ ነው።

- የምናያቸው ነገሮች ሁሉ መጀመሪያ አላቸው?
- አዎን አላቸው።

- የማናያቸው ነገሮች ሁሉ መጀመሪያ አላቸው?
- አዎን አላቸው።

- ከመጀመሪያ በፊት ሕይወት ምን ይመስል ነበር?

- ከመጀመሪያ በፊት ወንዞችና ሐይቆች ነበሩ?
- አልነበሩም።

- ከመጀመሪያ በፊት ተራሮችና ዛፎች ነበሩ?
- አልነበሩም።

- ከመጀመሪያ በፊት ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብት ነበሩ?
- አልነበሩም።

- ከመጀመሪያ በፊት እንስሳትና ወፎች ነበሩ?
- አልነበሩም።

- ከመጀመሪያ በፊት ሰማይና ምድር ነበሩ?
- አልነበሩም።

- ከመጀመሪያ በፊት እነዚህ ሁሉ ካልኖሩ፥ ሰዎች ነበሩ ተብሎ ይታሰባል?

- አይታሰብም።

- ሐይቆች ዛፎች ፀሐይ ሰማይና ምድር ከመጀመሪያ በፊት ካልኖሩ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ?

- አይችሉም።
- ከመጀመሪያ በፊት ነጭ ወይም ጥቁር ሕዝብ ነበር?
- አልነበረም።

- ከመጀመሪያ በፊት መናፍስት ነበሩ?
- አልነበሩም።
- ከመጀመሪያ በፊት ምንም ነገር አልነበረም።

- እስቲ የእግዚአብሔርን የመጀመሪያ ቃል ከመጽሐፉ ውስጥ እናንብብ፡

- «በመጀመሪያ እግዚአብሔር። »
- የመጀመሪያ የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረው ምንድን ነው?

- የመጀመሪያ የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረው ከመጀመሪያ በፊት እግዚአብሔር ብቻ መኖሩን ነው።

- ከመጀመሪያ በፊት ብቻውን ይኖር የነበረው ማን ነው?
- እግዚአብሔር ነው።

- ከመጀመሪያ በፊት እግዚአብሔር ብቻውን ከኖረ ከሁሉም የሚበልጠው ማን ነው?

- እግዚአብሔር ነው።
- እግዚአብሔር ከወንዞችና ከሐይቆች ይበልጣል።



- ለምን?
- ምክንያቱም ከመጀመሪያ በፊት የነበረው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር ከተራሮችና ከዛፎች ይበልጣል።

- ለምን?
- ምክንያቱም ከመጀመሪያ በፊት የነበረው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር ከፀሐይ ከጨረቃ እና ከከዋክብት ይበልጣል።

- ለምን?
- ምክንያቱም ከመጀመሪያ በፊት የነበረው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር ከመሬትና ከሰማይ ይበልጣል።

- ለምን?
- ምክንያቱም ከመጀመሪያ በፊት የነበረው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር በዓለም ካሉት ሰዎች ሁሉ ይበልጣል።

- ለምን?
- ምክንያቱም ከመጀመሪያ በፊት የነበረው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር በዓለም ከሚገኙት መናፍስት ሁሉ ይበልጣል።

- ለምን?
- ምክንያቱም ከመጀመሪያ በፊት የነበረው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው።

- ስለ መጀመሪያ እውነቱን ሊነግረን የሚችለው ማን ነው?

- እግዚአብሔር ነው ምክንያቱም ከመጀመሪያ በፊት የነበረው እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው።